**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!**

## ገብርኄር- የዐቢይ ጾም ስድስተኛው ሳምንት

የዐቢይ ጾም ስድስተኛ ሳምንት ገብርኄር ሲባል ትርጉሙም **ቸር አገልጋይ፤ ታማኝ አገልጋይ** ማለት ነው። የዚህን አገልጋይ ታሪክና ታማኝ ያስባለውን ምግባር **በማቴ. 25÷14-30** ላይ እናገኘዋለን። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ወንጌል ስለታማኙ አገልጋይ ካስተማረው ትምህርት በመነሳት አባታችን ቅዱስ ያሬድ ለዚህ ሰንበት በደረሰዉ መዝሙሩ **"መኑ ውእቱ ገብርኄር ወምዕመን....?"** ሲል ይጠይቃል። "በጎ ሥራ እየሠራ ጌታዉ የሚያገኘው ቸርና የታመነ አገልጋይ ማነው? ባለው ሁሉ ላይ የሚሾመው ደግሞም እግዚአብሔር በጥቂቱ ታምነሃልና በብዙ እሾምሃለው የሚለው ማነው?" ማለት ነው። በዚህ ሳምንት የሚሰበከው ምስባክ ይህ ነው፡-

**"ከመ እንግር ፈቃደከ መከርኩ አምላኪየ፥**
**ወሕግከኒ በማዕከለ ከርሥየ፥**
**ዜኖኩ ጽድቀከ በማኅበር ዐቢይ።"**
**መዝ. ፴፱÷፰-፱**

**"አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፥**
**ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው፥**
**በታላቅ ጉባኤ ጽድቅህን አወራሁ።"**
**መዝ. 39÷8-9**

በወንጌሉ ላይ አምስት መክሊትም የተቀበለው ሄዶ ነገደበት ሌላም አምስት አተረፈ፤ እንዲሁም ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ። አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቆፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ። **ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው።** አምስት መክሊት የተቀበለውም ቀረበና ሌላ አምስት መክሊት አስረክቦ። ‹‹ጌታ ሆይ፥ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት ›› አለ። ጌታውም **‹‹መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባርያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ››** አለው። ሁለት መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ። ‹‹ጌታ ሆይ፥ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍኩበት›› አለ። ጌታውም **‹‹መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝም ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታ ደስታህ ግባ››** አለው። አንድ መክሊት የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ። ‹‹ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህበትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፥ መክሊትህ እነሆ›› አለው። ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው፡- **‹‹አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ ካልዘራሁበት እንዳጭድ ካልበተንሁበትም እንድሰበስብ ታውቃለህን?** ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር። ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት ዐሥር መክሊትም ላለው ስጡት ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤.... የማይጠቅመውንም ባሪያ 'በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል´ እንዳለ የሚያሳስብ ነው።

**ባለ ጸጋ የተባለው ጌታ** ነው። **መክሊት የተባለው ደግሞ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ስጦታ** ነው። **በሦስቱ አገልጋዮች የተመሰልን** ደግሞ የክርስቶስ አካላት የተባልን እኛ **ምዕመናን** ስንሆን ለእያንዳንዳችን የተለያየ ስጦታ ተሰጥቶናል፤ **እንደየአቅማችን አምስት፣ ሁለት እና አንድ መክሊት**። በዚህ በተሰጠን ስጦታ ልናገለግልበት ያስፈልጋል። **ያተረፉት በሚገባ በታማኝነት ያገለገሉ ቅዱሳን ሰዎች** ሲሆኑ **መክሊቱን የቀበረው ደግሞ በታማኝነት በተሰጠው ጸጋ ማገልገል ሲገባው ያላገለገለ ሰው ነው**። በአምስተኛው ሳምንት /በደብረ-ዘይት/ ጌታ እንደሚመጣ ሲመጣ ደግሞ ለሁሉም እንደየሥራው እንደሚከፍል ተምረናል። አሁንም ነገሩን አጽንኦት ሲሰጥ **"ጌታቸው ሊቆጣጠራቸው መጣ"** በማለት ጌታችን በዕለተ ምጽአት ለኹሉም በሠራው ምግባር መጠን ዋጋ ለመስጠት እንደሚመጣ ያሳስበናል። የታመኑትን አገልጋዮች ሁለትም ያትርፉ አምስት ስለድካማቸዉ አብዝቶ እንደሚከፍላቸው ከወንጌሉ እንማራለን **‹‹መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝ ባሪያ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታ ደስታህ ግባ››** ። ነገር ግን በተሰጠው ጸጋ የማያገለግል ሁሉ ደግሞ የሃኬተኛ ባሪያ-የኃጥአንም ምሳሌ ነው። የዚህ ሰው ጥፋቱ ለማትረፍ አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን የተሰጠውን መክሊት መቅበሩ ነው፤ በዚህም ሳያበቃ ይህ ሰው አለመሥራቱ ጥፋት መሆኑን አምኖ መመለስ ሲገባው ጌታውን "ካልዘራህበት የምታጭድ ካልበተንህበት ምትሰበስብ" እያለ ሲወቅስ እናገኘዋለን። **እኛንም በጥፋታችን እግዚአብሔርን ከመውቀስ ይልቅ በንስሓ መመለስን ያድለን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።**

በተጨማሪ **መክሊት ቃለ እግዚአብሔር** ነው። የሰማነውን ቃለ እግዚአብሔር ለሌላው ማሰማት ይገባናል። ከእኛ የሚጠበቀው ማሰማቱ ብቻ ነው፤ በልቦና አድሮ ሥራን የሚሠራ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነውና። በአጠቃላይ በዚህ ሳምንት የሚሰጡ ትምህርቶች መሠረታዊ ዓላማቸው ክርስቲያኖች ሁላችን ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ከካህን እስከ ምዕመን በታማኝነትና በቅንነት ሆነን **በተሰጠን መክሊት እንድናተርፍበት ሠላሳ፣ ስድሳና መቶ ያማረ ፍሬ እንድናፈራበት መምከር ማስተማር ነው።** ስለዚህ ባለመክሊት የተባልን ምዕመናን በተሰጠን ጸጋ ወጥተን ወርደን፤ ጾመን ጸልየን፤ ሃይማኖታችንን አጽንተን እና ምግባራችንን አቅንተን በመክሊታችን ልናተርፍ ይገባል። **ሩቅ ሀገር ወደ ተባለ ወደ ሰማየ ሰማያት በክብር ያረገው የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ** በኋለኛው ዘመን ተመልሶ ዓለምን ለማሳለፍ ለእያንዳንዱ እንደሥራው ሊከፍል በክብር ሲመጣ ሁላችን በተሰጠን ጸጋና መክሊት አትርፈን እንድንገኝ **"እናንተ መልካም አገልጋዮች ወደ አባቴ መንግሥት በሐሴት ግቡ" የሚለውን የሕይወት ቃል እንድንሰማ እሱ ባለቤቱ መድኃኔዓለም ይርዳን! አሜን! ።**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!!!**
**የቅዱስ ጳውሎስ ሕክምና ግቢ ጉባኤ ትምህርት ክፍል መጋቢት ፲፰፣ ፳፻፲፭ ዓ.ም**